# ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ መሆኑ በተመለከተ የተከናወ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2017 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ማውጫ


ማውጫ i

የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (Executive Summary) I

ክፍል አንድ 1

መግቢያ ........ 1

የተቋሙ አመሰራረት፤ ........ 1

የተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ፣ ........ 2

ራዕይ ........ 2

ተልዕኮ ........ 2

የተቋሙ ስልጣንና ተግባር፤ ........ 2

የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 አንቀፅ 32 የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ........ 3

የተቋሙ አደረጃጀት እና የው ኃይል፤ ........ 5

የተቋሙ አደረጃጀት፤ ........ 5

**የሰው ኃይል፤** ........ 5

የተቋሙ የፋይናንስ ምንጭ፤ ........ 5

**በውጭ እርዳት ሰጪ ተቋማት የሚደረጉ ድጋፎች** 6

የኦዲቱ ዓላማ ........ 7

የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) ........ 7

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ........ 7

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) ........ 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 8

**የኦዲቱ ወሰን፤** 8

የሥራ ሂደት መግለጫ (Process description) ........ 8

ክፍል ሁለት 9

የኦዲት ግኝቶች፤ 9

2.1 አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ ........ 9

የህግ ማዕቀፍ በማውጣት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ .......... 9

በራስ ተነሳሽነት የሚከናወኑ ምርመራዎችን በተመለከተ፤ .......... 10

አስተዳደራዊ በደል መፈጸሙ ሲረጋገጥ ተገቢውን የመፍትሄ ሀሳብ መቅረቡንና አስፈጻሚ አካላት ተግባራዊ ማድረጋቸው ማረጋገጡን በተመለከተ .......... 11

በተለይ በሕጻናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት መጠናቱን በተመለከተ፣ .......... 14

2.2. ተቋሙ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እና መረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ .......... 16

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ መኖሩን በተመለከተ .......... 16

በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን በሚመለከት ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፣ .......... 18

ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫና ሥልጠና መገምገሙን በተመለከተ .......... 19

የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች መሰራጨታቸውን እና ግንዛቤዎቹ ያስገኙትን ውጤት በየጊዜው መገምገሙን በተመለከተ፤ .......... 20

ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ .......... 21

ክፍል ሶስት 23

መደምደሚያ 23

ክፍል አራት 25

የማሻሻያ ሀሳቦች 25

አባሪ 1፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ድርጅታዊ መዋቅር /Organizational Structure/.......... i

**አባሪ-2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት** iv

አባሪ 3፡ መጠይቅ የቀረበላቸው መ/ቤቶች ዝርዝር vi

## የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (Executive Summary)

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ እና ስኬታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የአሠራር ችግሮች ካሉ ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡ ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) "በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ አስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም፡ የሚል ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ማህበር (INTOSAI) የክዋኔ ኦዲት ስታንዳርድ እና በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2014 ዓ.ም እስከ የ2017 ግማሽ በጀት ዓመት ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሲሆን፣ በናሙና የተመረጡ የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲሁም የመንግሥት አስፈፃሚ መ/ቤቶች በተጨማሪም በናሙና የተመረጡ ባለድርሻ አካላት ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን ነው፡፡ በኦዲቱ ወቅት የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ክፍተቶች ታይተዋል፡-

- ✓ የተቋሙ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 እንዲሁም እና በ2016 ዓ/ም የወጣውን የተቋሙን ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1307/2016 የተዘጋጀውን ማስፈጸሚያ ረቂቅ ደንብ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፣
- ✓ ተቋም አሰራሩና አግልግሎት አሰጣጡ በተሟላ መልኩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ICT) ለማስደገፍ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል በተከፈለ ብር **7,541,016.21** የተዘረጋው በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ የሚመዘገብበት ሲስተም ማለትም (Case management System) አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣
- ✓ በ2012 ዓ.ም የጥሪ ማዕከል (Call Center Hosting Service Contract) የኢትዮ ቴሌኮም እና ከህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ከቻይና ከመጣ ተቋም IPCC (Internet Protocol Contact Center) የሚባል የጥሪ ማዕከል (7502) አገልግሎት ለማግኘት በብር **1,078,743.59** ውል ተዋውሎ ወደ ተቋሙ ያስገባ ቢሆንም ተቋሙ

ባለሙያ በመመደብ ማዕከሉን እየተጠቀመበት አለመሆኑ፣ ይህ ሥርዓት በ2015 ዓ.ም Web-Sprix በተባለ አገር በቀል ሶፍት ዌር አምራች የተመረተ IP-PBX (9503 ነፃ የስልክ ጥሪ) የተባለ የጥሪ ማዕከል ተግባራዊ ማድረጉን ግን አገልግሎቱ የሚቆራረጥ መሆኑ፣

- ✓ ተቋሙ ግንዛቤ ለመስጠትና ግንዛቤ ለመፍጠር ከተለያዩ የክልልና የአካባቢ ሬድዮ ጣቢያዎች ጋር ውል በመግባት እንዲሁም የተሌዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም የሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ያስገኙት ውጤት ያልተገመገሙ መሆኑን፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ ሊሆን የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች

- ✓ ተቋሙ በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው የተዘጋጀውት ረቂቅ ደንብ እንዲጸድቁ በየጊዜው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ሊያስብና ሊከታትለ የሚገባና ከተዘጋጀ አምስት አመት የሆነው ረቂቅ ደንብን ደግሞ በተሻሻለው የተቋሙ አዋጅ መሰረት በፍጥነት በማሻሻልና የባለድርሻ አካላትን ግብዓት በማሰባሰብ እንደገና ለምክርቤቱ በመላክ ሊያጸድቅና ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
- ✓ አሰራሩና አግልግሎት አሰጣጡ በተሟላና ዘመናዊ ለማድረግ የተዘረጋውን በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ የሚመዘገብበት ሲስተም ማለትም (Case management System) አገልግሎት በሙሉ ኃይሉ በሁሉም ቅርንጫፎች ወደ ትገበራ ሊያስገባ እንዲሁም የአቤቱታና ቅሬታ መቀበያ የነጻ ጥሪ አገልግሎትም የ24 አገልግሎት እንዲሰጥ በተፈላጊው የሰው ኃይል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሟሟላት ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
- ✓ በዜጎች ላይ የአስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ ለህብረተሰቡና ለአስፈፃሚ አካላት/ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት በአመታዊ እቅዱ ላይ በማካተት እና የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት ለህብረተሰቡም ግንዛቤ ማስጨበጥና የተለያዩ የስልጠና ማዋሎችን በማዘጋጀት የሚሰጣቸውን ሥልጠና እና ግንዛቤዎች ስገኙትን ፋይዳ ሊገምግም፣ ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ጠንካራ ጎኖቹ የሚጠናከሩበት ደካማ ጎኖቹም የሚስተካከሉበትን ሁኔታዎች ሊያመቻቻል ይገባል፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለህብረተሰቡ አገልግሎት ለመስጠት ነው የተቋቋሙት፡፡
2. ይህንን አገልገሎት ለመስጠት ደግሞ ግልጽ የሆነ አሰራር በመዘርጋትና ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች ሊያሳውቁና በአወጡት መስፈርት መሰረት አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዜጎች የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት ሲሄዱ ለሚያጋጥማቸው የአስተዳደራዊ በደል አቤቱታዎችን ተቀብሎ በመመርመር ለሚመለከታቸው አካላት የመፍትሄ ሀሳብ የሚያቀርብ ገለልተኛ አካል ያስፈልጋል፡፡
3. ከዚህ በተጨማሪ ይህ ገለልተኛ አካል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥራቸውን ለማከናወን የሚያወጡት መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አሰራሮች ህገ-መንግሥቱን የማይቃረኑ መሆኑን መከታተል፤ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ነባር ሕጎችና አሰራሮች እንዲሻሻሉ፤ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ማሳሰብንና ልዩ ትኩረት የሚሹ ዜጎች የተሳታፊነትና ተጠቃሚነት መብት እንዲረጋገጥ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## የተቋሙ አመሰራረት፤

4. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/15/ መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 211/92 ተቋቋመ፡፡ በመቀጠልም ሥልጣንና ተግባሩ በ1142/2011 እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ የተቋሙ ዓላማ በህግ የተደነገጉ የሰዎች መብቶችና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካል መከበራቸውን በማረጋገጥ የህግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡ ተቋሙ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው የሚሰጧቸውን ውሳኔዎችና አሠራሮቻቸው የሰዎችን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችንና ሕጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን እንዲሁም ሥራቸውን በሕግ መሠረት የሚያከናውኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶታል ፡፡
5. ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠዉ ስልጣንና እና ተግባር በተጨማሪ የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 አንቀፅ 32 ላይ ያሉትን ድንጋጌዎች እንዲያስተገብር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## የተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ፣

### ራዕይ

6. “በ2017 ዓ.ም ፍትሃዊና ተጠያቂነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን በማድረግ ተዓማኒ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሆኖ መገኘት” ነው፡፡

### ተልዕኮ

7. በአስፈፃሚ አካላት የሚወጡ መመሪያዎች፣ውሳኔዎችና አሰራሮች ህገ-መንግሥቱን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር፤ አስተዳደራዊ በደል አቤቱታዎችን በመመርመር የመፍትሄ ሀሳብ መሻት፤ነባር ሕጎችና አሰራሮች እንዲሻሻሉ እና አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ማሳሰብ፤አስተዳደራዊ በደልን ለመከላከል የቁጥጥርና ጥናት ስራዎችን በማካሄድ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ፤በመልካም የመንግሥት አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ለመንግሥት የምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እና የመረጃ ነፃነት ህጉን ተግባራዊነት በመከታተል መልካም የመንግሥት አስተዳደርን ማስፈን፤ ነው፡፡

## የተቋሙ ስልጣንና ተግባር፤

8. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1142 /2011 አንቀጽ 7 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥተውታል ፡-

- አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ የሚሠጧቸው ውሣኔዎች እና አሠራሮቻቸው ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን እንዲሁም ሌሎች ህጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር ፣
- የቀረቡለትን የአስተዳደር በደል አቤቱታዎች መሰረት በማድረግ ወይም በራስ ተነሳሽነት ወይም በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ስልታዊ ምርመራ የማካሄድ ፣
- አስተዳደራዊ በደል መፈጸሙን ሲያረጋግጥ ተገቢውን የመፍትሄ ሀሳብ የማቅረብ
- አስፈፃሚው አካል ሥራውን በሕግ መሠረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥ እና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ ፣
- አስተዳደራዊ በደሎች የሚቀረፉበትን ሁኔታ የማጥናት እና ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ፣
- የተሻለ የመንግሥት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ሕጎች ወይም አሠራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፣አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ ፣

- በመልካም የመንግሥት አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ለመንግሥት የምክር አገልግሎት የመስጠት፣
- ሕብረተሰብ ስለ መልካም አስተዳደር እና ስለ አስተዳደራዊ ፍትህ ግንዛቤ እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር ፣
- በዓለም አቀፍ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች በሚመለከት ስብሰባዎች ኮንፍረንሶች ሲምፖዚየም ላይ መሳተፍ ፤
- የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነጻነት ህግ ክፍል ሶስት ተግባራዊ ስለመደረጉ መከታተል እና መቆጣጠር፣
- ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፣

ስልጣንና ተግባር ተሰጥተዉታል፡፡

## የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 አንቀፅ 32 የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት

አንቀጽ 32 የህዝብ ዕንባ ጠባቅ ተቋም ኃላፊነቶች

32/1 የህዝብ ዕንባ ጠባቅ ተቋም በዚህ አዋጅ የክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ለመጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ልረዳው የምችል አኳኋን፡-

ሀ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዋች አላማዎች

ለ/ በዚህ አዋጅ የሚሸፈን የመንግስት አካላት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች እና የምክትሎቻቸው ሙሉ ስምና አድራሻ

ሐ/ የእያንዳንዱን መንግስት አካላት አብይ የስራ ፀባይ

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሰረት የሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች የሚቀርቡበት ፎርም፣

ሠ/ መረጃ ጠያቂዎች በዚህ አዋጅ ክፍያ ሶስት መሰረት ከህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የሚደረግላቸውን ትብብር ወይም አገልግሎቶች፣

ረ/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከህዝብ እንባ ጠባቅ ተቋም ለመረጃ ጠያቂዎች የሚሰጡ እገዛ ወይም አገልግሎት

ሸ/ በዚህ አዋጅ በክፍል ሶስት ድንጋጌዎች የተመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች ባልተከበሩ ጊዜ በአዋጅ የተበጁ መፍትሄዎች

ቀ/ ስለ አተዳደራዊ ይግባን አቀራረብ

በ/ የህዝብ ግንኙነት ወይም የመንግስት አካላት ሃላፊዎችን ውሳኔ በመቃወም ለፍርድ ቤቶች ስለሚቀርብ የይግባኝ ማመልከቻዎች

ተ/ በዚህ ክፍል በመንግስት አካላት ታትመው እንዲወጡ የታዘዙ መረጃዎች አይነቶችና እነዚህን መረጃዎችን ለማግኘት የሚረዱ ማስረጃዎችን፣

ቸ/ መረጃ ክፍያ ስለሚከፍልባቸውና ከክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ስለማድረግ ጥያቄዎችን፣ እና

ነ/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች የዚህን ክፍል ድንጋገዎችን በተመሳሳይ መንገድ እንዲፈፅሙ ለማድረግ የሚወጡ የአፈጻጸም መመሪያዎችን እና ማብራሪያዎችን የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት በስራ ላይ ከሚውሉ ቀን ጀምሮ ባሉት 18 ወራት ግዜ ውስጥ በመንግስት አፊሲያላዊ ቋንቋዎች አትሞ የማውጣት ሃላፊነት አለበት፡፡

32/2. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት በተጨማሪ አቅም በፈቀደ መጠን፡-

ሀ/ በአንቀፅ 36(1) የተቀበላቸውን ሪፖርቶች መሰረት በማድረግ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች በመንግስት አካላት መፈጸማቸውን የመከታተልና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፣

ለ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አፈፃፀም አስመልክቶ አሰራሮችን ለማዳበር እና ለማሻሻል የሚረዱ አጠቃላይና ወይም ዝርዝር ውሳኔ ሀሳቦችን ለመንግስታዊ አካላት የማቅረብ፣

ሐ/ መረጃ የማግኘት መብትና የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ውጤታማ አፈፃፀም አስመልክቶ ለህዝብ ግንኙነት ሀላፊዎች የሚሰጡ ስልጠናዎች የማዘጋጀት ወይም የማገዝ፣

መ/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የሚጠየቁ መስፈርቶችንና ግለሰቦች ያላቸውን መብት ለህዝብ የማሳወቅ

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 መሰረት ታትመው መውጣት ያለባቸውን መረጃዎች በተመለከተ ከስራ ባህሪያቸው የተነሳ በአንድ ህትመት ውስጥ መረጃዎቻቸውን አጣምረው ማውጣት ያለባቸውን የመንግስት አካለት ወይም የህትመት ወጪን መጋራት የሚኖርባቸውን የመንግስት አካለት ወይም ወጪያቸው በሌላ የመንግስት አካል ሊሸፈንላቸው የሚገባ የሚመለከቱ ውሳኔዎችን የመስጠት፣

ረ/ የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ድንጋጌን አጠቃቀም ግልጽ ለማድረግ የሚያግዙ የማብራሪያ መድብሎችን ማዘጋጀት፣

ሰ/ የዚህን አዋጅ ክፍል ድንጋጌዎቸ ለማሻሻል፣ ለማጠናከር እና ለማዳበር የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፣ እና

ሸ/ ለዚህ ክፍል ድንጋጌዎች አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፣ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው፡፡

32/3. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችለው የተሟላ ስልጣን ያለው ሲሆን ለስራው የሚስፈልገውን ተጨማሪ በጀትም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያገኛል፡፡

32/4. ዋና እንባ ጠባቂው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## የተቋሙ አደረጃጀት እና የው ኃይል፤

### የተቋሙ አደረጃጀት፤

9. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን በተቋሙ የዕንባ ጠባቂ ጉባኤ፣ ዋና ዕንባ ጠባቂ፣ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ፣ የህጻናት ሴቶች አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ጉዳዮች ዕንባ ጠባቂ፣ የ8 ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዕንባ ጠባቂዎች፣ የዋና ዕንባ ጠባቂ ጽ/ቤት ኃላፊ እና በ17 ዳይሬክተሮች ተዋቅሮ ተደራጅቷል፡፡ ***ድርጅታዊ መዋቅሩ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ (1) ተያይዟል፡***

**የሰው ኃይል፤**

10. በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም እስከ ታህሳስ 30/2017 ዓ.ም ያለው የሰው ኃይል የሴት ሰራተኞች ብዛት 60 (46.2%) እና የወንድ ሰራተኞች ብዛት 70 (53.8%) በድምሩ 130 ሰራተኞች ይገኛሉ፡፡ በዚህ ወቅት ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ማስተርስ ዲግሪ ወንድ 13(10%) ሴት 6 (4.6%) ድምር 19፣ ቢ. ኤ ዲግሪ ወንድ 32 (25%) ሴት 29 (22.3%) ድምር 61፣ ዲፕሎማ ወንድ 2 (1.53%) ሴት 15 (11.53%) ድምር 17 እና ከዲፕሎማ በታች ወንድ 23 (18%) እና ሴት 10 (8%) በድምሩ 33 ናቸው፡፡

### የተቋሙ የፋይናንስ  ምንጭ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግሥት ከሚመደብ በጀት ሲሆን በተጨማሪ በውጭ እርዳታ ሰጪ ተቋማት የሚደረጉ ድጋፎች ያሉት ሲሆን ከ2014 እስከ 2017 (የአንደኛ ሩብ ዓመት) የተመደበለትን በጀትና ከ2014 ዓ/ም እስከ መጋቢት 2016 በጀት ዓመት (IPF፣ UNDIP፣ UNICEF፣ UNISCO፣ UNDP፣ HOC) የውጭ እርዳታ ድጋፍ  ያገኘው ፋይናንስ  በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**መደበኛ በጀት**

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 85,068,000.00 | 81,107,007.00 | 95.34 % |
| 2015 | 95,009,129.00 | 93,377,018.00 | 98.3 % |
| 2016 | 95,063,714.2 | 94,117,714.03 | 99 % |
| 2017 የሦስት ወር | **25,726,344** | **21,957,299.** | **85.40%** |

**በውጭ እርዳት ሰጪ ተቋማት የሚደረጉ ድጋፎች**

IPF

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 39,569,521.91 | 37,831,910.68 | 95.6 % |
| 2015 | 45,947,000.00 | 46,923,886.27 | 102.13% |
| 2016 | 34,000,000.00 | 33,323,748.22 | 98.01% |
| 2017 | - | - | - |

UNDIP

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 1,309,171.12 | 1,511,348.18 | 115.4% |
| 2015 | - | - | - |
| 2016 | - | - | - |
| 2017 **(የአንደኛ ሩብ አመት)** | **1,711,260** | **1,711,260** | **100%** |

UNICEF

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| **2014** | **819,031.00** | **819,031.00** | **100%** |
| **2015** | **1,413,119.07** | **1,105,255.13** | **78.21%** |
| **2016** | **636,700.15** | **636,700.15** | **100%** |
| **2017 (የአንደኛ ሩብ አመት)** | **510,799.08** | **510,790.08** | **100%** |

UNISCO

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 6,866,541.00 | 6,866,541.00 | 100% |
| 2015 | 0 | 0 | |
| 2016 | 0 | 0 | |
| 2017 | 0 | 0 | |

- ✓ **ማሳሰቢያ፡- ይ UNISCO በ2014 በጀት ዓመት ብቻ ነው እርዳታ ያደረገው፡፡**

## የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ እና ስኬታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የአሠራር ችግሮች ካሉ ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) "በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ አስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም፡ የሚል ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

13. የተለየው የክዋኔ ኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት ሁለት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፡-
    1. የአስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም
    2. ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር የአስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እና መረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን መገምገም

    የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

14. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመገምገም የሚያስችል 21 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት በዋናነት መሰረት የሆኑት ለአስተዳዳራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራና ምላሽ አሰጣጥ

በተመለከተ የወጣ አዋጅ 1142/2014፣ የተቋሙ የአምስት አመት (2013-2017) ና የአስር ዓመት (2013-2022) ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተቋሙ የዜጎች ቻርተር፣ የቁጥጥር አሰራር ማንዋል፣ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15. ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ማህበር (INTOSAI) የክዋኔ ኦዲት ስታንዳርድ እና በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2014 ዓ.ም እስከ የ2017 ግማሽ በጀት ዓመት ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰን፤**

16. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሲሆን፣ በናሙና የተመረጡ የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲሁም የመንግሥት አስፈፃሚ መ/ቤቶች በተጨማሪም በናሙና የተመረጡ ባለድርሻ አካላት ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን ነው፡፡ ዝርዝሩ አባሪ 3 ላይ ተያይዟል፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process description)

17. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ መመሪያ ክፍል የስራ ሂደት መግለጫ/Process description/
    - በተቋሙ ስር በሚወድቁ ጉዳዩች ላይ አቤቱታ/ጥቆማ ይቀበላል፣
    - በቀረቡ ጥቆማዎች ላይ ምርመራ ማካሄድ የመፍትሄ ሀሳብ/ውሳኔ መስጠት ተከትሎ ማስፈፀም
    - በመርማሪ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ሲኖር የመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ ማየት፤
    - የምርመራ ሥራ የሚመራበትን ማኑዋል ያዘጋጃል፣ በዋና ዕንባ ጠባቂ ሲጸድቅ ተግባር ላይ ማዋል፤
    - በዋና ዕንባ ጠባቂ የተመሩ የራስ ተነሳሽነት እና የስልታዊ ምርመራ ስራዎችን ማከናወን ፤
    - ለተቋሙ ሥራ የማይተባበሩ አስፈፃሚዎች ላይ ክስ እንዲመሰረት ለዋና ዕንባ ጠባቂ ሀሳብ ያቀርባል፣ሲፈቀድም አስፈላጊውን መረጃ ለፖሊስ ማቅረብ ፤
    - በዉስብስብ ጉዳዮች ላይ የኬዝ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ መድረክ ማዘጋጀት፤
    - የዳይሬክቶሬቱን የሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ወቅታዊ ሪፓርትም ለዋና ዕንባ ጠባቂ ማቅረብ ፤

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች፤

### 2.1 አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

**የህግ ማዕቀፍ በማውጣት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤**

18. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የህግ ማዕቀፍ ማለትም ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

19. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለው

- የተቋሙ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 ማስፈጸሚያ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በደብዳቤ ቁጥር ዕንባ/ዘ1-100/መ30/2 በቀን ሐምሌ 2 ቀን 2012 የተላከ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፣
- በ2016 ዓ/ም የወጣውን የተቋሙን ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1307/2016 ጸድቆ የወጣው በሚያዝያ 2016 ሲሆን ይህንን ተከትሎ ማስፈጸሚያ ደንብ ተዘጋጅቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት አስፈላጊው ግብዓት ተሰብስቦ ደንቡ ለምክር ቤት የተላከ መሆኑን የተገለጸ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ደንቡ ያልጸደቀ መሆኑን፣
- አዋጅ 590/2000 በተመከከት ለህዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ ስለማድረግ የወጣ ደንብ ለተለያዩ መረጃዎች የአገልግሎተት ክፍያ ተመን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 428/2010 እና ደንብ ቁጥር 405/2009 ጸድቀው ስራ ላይ መዋላቸውን፣
- የመረጃ ነፃነት መብት ትግበራ፣ የሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ የአፈፃፀም መመሪያ፣ የዕንባ ጠባቂ ተቋም የሰነዶች አጠባበቅ፣ አሰተዳዳር እና አወጋገድ የተግባር መመሪያ፣ እና የመረጃ ነፃነት መብት የቅሬታ ማስተናገጃ የአፈፃፀም መመሪያ፣ የተሻሻለ የቁጥጥር አሠራር መመሪያ፣ የምርመራ አመራር ማንዋል፣ የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል እማ

ግምገማ ለማድረግ የተዘጋጀ ማንዋል፣ ተዘጋጅተው እና ጸድቀው ስራ ላይ መዋላቸውን፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

20. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄና እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት ላይ በሰጡት ምላሽ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 እና በአዋጅ ቁጥር 1307/2016 ስለተሻሻለ ሌላ ደንብ አዘጋጅተን ለምክር ቤት ሊቀርብ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

21. ተቋሙ ሥራውን ግልጽ የተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሚያስፈልጉ ደንቦችና በወቅቱ ተዘጋጅተው አለመጽደቃቸው፣ አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ ለማቅረብ የሚመጡ ዜጎችን ተገቢውን መፍትሄ መስጠት አዳጋች ከማድረጉም በላይ በተቋሙ የሚከናወን ተግባር ቀላልና ለአሰራር ምቹ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## በራስ ተነሳሽነት የሚከናወኑ ምርመራዎችን በተመለከተ፤

22. ተቋሙ በራስ ተነሳሽነት አስተዳደራዊ በደል ላይ ስልታዊ ምርመራ ሊያካሂድ ይገባል፡፡

23. በኦዲቱ ወቅት

- ✓ ተቋሙ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1142/2014 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በራስ ተነሳሽነት በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ምርመራ ለማከናወን ሥርዓት የዘረጋ መሆኑ፣
- ✓ በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ላይ በራስ ተነሳሽነት በየካቲት 2014 ምርመራ አከናውኖ የመፍትሔ ሃሳብ ለተቋሙ የላከ መሆኑ፣
- ✓ በትምህርት ሚኒስቴር እና ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ኤጀንሲ ላይ ከሚዲያ በተገኘ ጥቆማ የራስ ተነሳሽነት ምርመራ መከናወኑ ቢገለጽም መረጃው በመቼ ዓ.ም እንደተከናወነ እና ውጤቱ ለሚመለከተው አካል ስለመቅረቡ የማያሳይ መሆኑ፣
- ✓ ተቋሙ በአስር ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት የተለያዩ አስተዳደራዊ በደሎችን በዋና መ/ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በራስ ተነሳሽነት ምርመራ ለማከናውን በየአመቱ ቢታቀድም በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያልተከናወነ መሆኑ፣

ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከተደረጉ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት ተችሏል፡፡

24. ስለሁኔታው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ በራስ ተነሳሽነት ምርመራዎችን የኦዲት ጊዜው በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥ 21 ጉዳዮች ላይ የራስ ተነሳሽነት ምርመራ የተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25. የተቋሙ የስራ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም የቀረበው ማስረጃ በራስ ተነሳሽነት ምርመራ ለማከናወን በየአመቱ ቢታቀድም የበጀት እጥረት ስለሚኖር ስራው በዕቅድ እንደማይከናውን ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የተገለጸ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

26. በመሆኑም ተቋሙ በተሰጠው ስልጣን ተግባር መሰረት በዕቅድ በመታገዝ የቀረቡለትን በራስ ተነሳሽነት በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ምርመራ አለማካሄዱ በተቋማት የሚታዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን አቤተቱ ከመቅረቡ በፊት በቅድሚያ ለመከላከልና ለማሻሻል የራሱን አስተዋጽኦ እንዳይወጣ አድርጎታል፡፡

## አስተዳደራዊ በደል መፈጸሙ ሲረጋገጥ ተገቢውን የመፍትሄ ሀሳብ መቅረቡንና አስፈጻሚ አካላት ተግባራዊ ማድረጋቸው ማረጋገጡን በተመለከተ

27. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም መፈጸማቸውን በምርመራና በማጣራት ላረጋገጣቸው አስተዳደራዊ በደሎችና ክፍተቶች እንዲፈቱ ወይም እንዲሻሻሉ የመፍትሄ ሀሳብ ሊያቀርብና ተግባራዊነታቸውንም ሊከታተል እና አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ያልወሰዱትን አስፈፃሚ ተቋማትን በልዩ ሪፖርት ለምክር ቤት ሊያቀርብና ለፍትህ ሚኒስቴርም ሊያሳውቅ ይገባል ፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለው ተቋሙ አስተዳደራዊ በደል መፈጸሙን ሲያረጋግጥ ተገቢውን የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም፣ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደል መፈጸሙን ሲያረጋግጥ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት በተቋሙ የተሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦች ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትል ሥራ አለመሰራቱ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

29. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስፈፃሚ አካላት በሚያከናውኗቸው ሥራዎች በሕግ መሠረት የሚያከናውኑ መሆኑን ለማረጋገጥ እና አስተዳደራዊ ጥፋቶች

እንዳይፈፀሙ ለመከላከል ቁጥጥር ለማድረግ የዘረጋውን ሥርዓት በአግባቡ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት፡-

- ✓ በቁጥጥር የሚለዩ የሕግ ክፍተቶች እና የአሰራር ክፍተቶች ተቋማቱ በተሰጣቸው ግብረ መልስ መሰረት ማስተካከላቸውን በድጋሚ ቁጥጥር የሚያረጋገጥ መሆኑ፣
- ✓ ተቋማቱ ማስተካከያ ባያደርጉ የሚወሰድ የተጠያቂነት ስርዓት አለመኖር፤
- ✓ የመንግሥት ተቋማት በተሰጣቸው የማስተካከያ ሀሳብ መሰረት አለመፈፀም በብዙዎቹ ላይ ስለሚስተዋል፣ አስተዳደራዊ በደሎች ሲፈፀሙ በደሎቹን መከላከልና ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ ያልተቻለ መሆኑ፤
- ተቋሙ አላስፈፅም ያለ አስፈፃሚ አካል በልዩ ሪፖርት ለምክር ቤቱ በልዩ ሪፖርት ቢቀርብም ለፍትህ ሚኒስቴር የማያሳውቁ  መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

30. ስለሁኔታው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ  በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ  እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ

- የአዋጁን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ የተቋሙ የምርመራ ማኑዋል ስለ መፍትሄ ሀሳብ አሰጣጥና ክትትል በዝርዝር ስርአቱን ያስቀመጠ መሆኑ፣
- ስራው እንዲከናወን  የስራ ክፍል እና ባለሙያ ተመድቦለት ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን
- የሚመጡ አቤቱታዎች አብዛኛዎቹ ከእኛ ስልጣን ውጪ የሆኑ ናቸው ከእኛ ስልጣን ጋር የሚገናኙትን መርምረን የመፍትሄ ሃሳብ እናቀርባለን ለምክር ቤትም ልዩ ሪፖርት እንደሚያቀርቡ፣
- የማይፈፅሙትን አስፈፃሚ ተቋማት ወደ ክስ እንወስዳለን በተጨማሪም
- ተቋሙ በአመት ከ200 ተቋማት በላይ ቁጥጥር እንደሚያደርግ በአስፈፃሚ ተቋማት ላይ የሚገኙ  ግኝቶች መስተካከላቸውን ድጋሜ ቁጥጥር ለማድረግ ስንሄድ የነበሩት ባለስልጣናት/ኃላፊ እየተነሱ ብዙ የስራ መጉላላት እንደሚያጋጥማቸው፣
- አቤት ባዮች በተቋሙ አዲስ የሥራ አመራር በመጣ ቁጥር ጉዳያቸውን በድጋሚ የማንሳት ነገር በተደጋጋሚ ያጋጥመናል፣

በዚህ ምክንያት ሊዘገይ ይችላል በማለት ገልፀዋል፡፡

31. የሥራ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም የኦዲት ቡድኑ ከ2014-2016 ዓ.ም ድረስ ያለው የተቋሙን እቅድ ክንውን በከለሰበት ወቅት በበጀት አመቱ በእቅድ ተይዘው በተያዘላቸው አመት ሳይከናወኑ ማለትም የመፍትሄ ሀሳብ ሳይሰጣቸው ወደ ሚቀጥለው ዓመት የሚሸጋገሩ አቤቱታዎች መኖራቸው እንዲሁም የተቋሙ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የተከናውነ የቁጥጥር ስራ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

32. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ነው ብሎ ያመነበትን የመፍትሄ ሀሳብ ሲያቀርብ በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የመንግስት አስተዳደር አካላት እርምጃ ካልወሰዱ የታሰበው የመልካም አስተዳደር በሁሉም አካባቢ ለማስፈን እየተደረገ ያለው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ እንዲሁም በመንግሥት ተቋሞች አስተዳደራዊ **አስተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት በማጥናት ተግባራዊ መድረጉን በተመለከተ።**

33. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ የሚያስችል ጥናት ሊያጠናና ውጤቱንም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

34. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አዋጅ ቁጥር 1142/2014 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 5 በተሰጠው ስልጣን መሰረት

- ተቋሙ አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ የሚያስችል ጥናት ለማከናወን የሚያስችል የጥናት አሠራር ማንዋል ያዘጋጀ መሆኑን፣
- በትምህርት ሚኒስቴር ላይ የአካል ጉዳተኞች ወደ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት የመግባት ምጣኔን ለማሳደግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በተመለከተ ሀገራዊ ጥናት በ2015 ዓ.ም. ያከናወነ መሆኑ፣
- በ2014 ዓ.ም በመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት ሰራተኞች አገልግሎት አሰጣጥ ተግዳሮቶች ዙሪያ የተደረገ ጥናት፣ በ2015 ዓ.ም በተቋሙ የተሰሩ የቁጥጥር ሥራዎች ያመጡት ውጤትና ፋይዳ ላይ የተደረገ ጥናት፣ የነዳጅ ድጎማ አፈጻጸም መመሪያ ያሉ ተግዳሮቶችና መንስኤዎች ዙሪያ የተደረገ ጥናት፣ መኖራቸው፣ በመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማት የመልካም አስተዳደር አፈጻጸማቸውን አስመልክቶ ጥናት ላይ በመመስረት በደረጃ መለየት በ2016 ዓ.ም በመንግሥት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት አሠጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችና መንስኤዎች በሚመለከት በድምሩ አምስት የጥናት ሥራዎች

ቢገለጽም የጥናቶቹ ሰነዶችና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲጠቀሙበት ስለመላኩ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተጨማሪም ሰባት የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በተቋሙ የተጠና ጥናት ስለመኖሩ አለማወቃቸውን ገልፀዋል፡፡

36. ስለሁኔታው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ከህዳር 2016 ዓ.ም. በፊት ባሉት ጊዜያቶች እያንዳንዱ የስራ ክፍሎች የጥናት ስራዎችን ሰርቷል ከህዳር 2016 ዓ.ም. ወዲህ ግን የሰራ ክፍል ተደርጎለት ብቻውን የጥናት ስራ የሚሰራ ክፍል አለው በማለት ገልጸዋል፡፡

37. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም ተከናውነዋል የተባሉ የተወሰኑት ጥናቶች ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተገበሩ የተላኩበት ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

38. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ የሚያስችል ጥናት በማጥናት በሚመለከታቸው አካላት እንዲተገበሩ ካልተደረጉ እንደ አገር በመንግሥት አስፈፃሚ ተቋማት የሚታዩ አስተዳደራዊ በደሎች በአግባቡና በማያዳግም ሁኔታ እንዳይፈቱና እንዲሁም በተቋሙ የሚታዩ የአስተዳደራዊ በደል አቀባበል፣ ምርመራ እንዲሁም ምላሽ አሰጣጥ የሚታዩ የአሰራር ግድፈቶችን በአፋጣኝ ለመቅረፍና የተሻሉ አሰራሮችን እንዳይመጣ ያደርጋል፡፡

## በተለይ በሕጻናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት መጠናቱን በተመለከተ፣

39. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተለይ በሕጻናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት በማስጠናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

40. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተለይ በሕጻናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል፣

- ✓ የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ማካተቻ ጋይድላይን እና

የሥልጠና ሞጁል በ2013 ያዘጋጀ መሆኑ፣

- ✓ ከ2014-2017 ድረስ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃት ተቀብሎ መፍትሄ ከመስጠት አንጻር አስፈጻሚው አካል የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በተመለከተ፣አካል ጉዳተኞች ወደ መጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የመግባት ምጣኔ ለማሳደግ በአስፈጻሚው አካል እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን አስመልክቶ ሃገራዊ ጥናት መከናወኑ፣
- ✓ ከአስፈፃሚ ተቋማት በ2016 ዓ.ም መረጃ የተሰበሰበ መሆኑ፤
- ✓ በአስተዳደር በደልም ይሁን በሴቶች፣ ህፃናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ከሚመለከታቸው ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት ወይም በቅንጅት እየሰራ ስለመሆነ ማስረጃ አለመቅረቡ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቃለመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

41. ስለጉዳዩ የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ጥናት መከናወኑን፣ በተቋሙ ከ2012-2017 ዓ.ም በስትራቴጂክ እቅዱ መነሻ በሕጻናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ብቻ ሳይሆን አረጋውያንን ጨምሮ የተከናወኑ የጥናት ስራዎችን እንዳሉ፣ ህጻናት የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችንና ቅሬታዎቻቸውን ወደተቋማችን የሚያቀርቡበት ስርአት አስመልክቶ፣ በድምሩ 3 ጥናቶች ተከናውነው በማለት ምላሽ ስጥተዋል፡፡
42. የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም ጥናቱ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተወያይተውበት ስለመጽደቁ ለሚመለከታቸው አካላት አሰራራቸውን እንዲፈትሹበት መላኩን የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የተሰጠውም ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡
43. በመንግስት በአስፈፃሚ ተቋማት በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች እንዲሁም በአረጋዊያን ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል ያስችል ዘንድ ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ባለማድረጉ በሴቶች፣ ህፃናት፣ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞች እንዲሁም አረጋዊያን የሚደርሱ አስተዳደራዊ በደሎች በህጉ መስረት እንደ ማንኛውም ህብረተሰብ በአፋጣኝ እንዳይፈቱ ያደርገዋል፡፡

## 2.2. ተቋሙ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እና መረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

### በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ መኖሩን በተመለከተ

44. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል አቀባበል፣ ምርመራና ምላሽ አሰጣጡ በተሟላ መልኩ በICT እንዲታገዝ ሊያደርግ ይገባል

45. ተቋሙ

- አሰራሩና አግልግሎት አሰጣጡ በተሟላ መልኩ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት (ICT) የተደገፈ አለመሆኑ፤
- ከአለም ባንክ በተገኘ የእርዳታ ገንዘብ በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ የሚመዘገብበት ሲስተም ማለትም (Case management System) የሚባል በገንዘብ ሚኒስቴር ተዋዋይነት ከ Technologies Connect Ltd in JV with T & T Consulting PLC ከሚባል ድርጅት ጋር ጁላይ 2022 ሲስተም ለመስጫን የተጫነው ሥርዓት እንደሚሰራ ተቋሙ ማረጋገጫ ሲያገኝ **ኮንትራክተሩ** 70% ማለትም ብር **5,278,711.35** እንደሚከፈለው፣ ለተቋሙ እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስራተኞችና በሲስተሙ ላይ ስልጠና ሲሰጥ ለመስጠት 100% ማለትም ብር 396,895.59 እንዲሁም የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ክፍያ 30% ለመክፈል በተገባው ውል መሰረት ብር 2,262,304.86 አጠቃላይ ከስልጠና ውጪ በድምሩ ብር **7,541,016.21** ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ የተገዛ ሲስተም በዋና መ/ቤቱ ሆነ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአግባቡ ስራ ላይ እየዋለ አለመሆኑ፤ በተጨማሪም
  - ✓ በተቋሙ የተዘረጋውን Case management Syste ሙሉ በሙሉ እየተጠቀመ አለመሆኑ፣
  - ✓ በተቋሙ እና በስምንት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ Case management Syste እንዲጠቀሙ አስገዳጅ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የሌለ መሆኑ፤
  - ✓ በአሁኑ ሰዓት ለተቋሙ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ሆነ የተሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦች Case management System እየተመዘገቡ አለመሆኑ፤
  - ✓ የተቋሙ ስምንቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በእኩል ደረጃ Case management System እየተጠቀሙ አለመሆኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ (Case management System) ላይ ስልጠና

ወስደው በሙከራ ላይ እንደሚገኙ የገለጹ ሲሆን፣ ይሁን እንጂ ሲስተሙ በኔትዎርክ መቆራረጥ ምክንያት ስራዎችን በተሟላ ሁኔታ መስራት አለመቻሉን መግለጻቸው፤

- ✓ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የህዝብ አቤቱታ መቀበያ እና ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎት መረጃ የሚያስተላልፍበት
  - ➢ በ2012 ዓ.ም የጥሪ ማዕከሉ Call Center Hosting Service Contract የኢትዮ ቴሌኮም እና ከህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ከቻይና ከመጣ ተቋም IPCC (Internet Protocol Contact Center) የሚባል የጥሪ ማዕከል (7502) አገልግሎት ለማግኘት በብር 1,078,743.59 ውል ተዋውሎ ሥራ የጀመረ ቢሆንም ከ2015 ጀምሮ የቆመ መሆኑ፣
  - ➢ በ2015 ዓ.ም Web-Sprix በተባለ አገር በቀል ሶፍት ዌር አምራች የተመረተ IP-PBX (9503 ነፃ የስልክ ጥሪ) የተባለ ሌላ የየጥሪ ማዕከል ተግባራዊ ቢያደረግም አገልግሎቱ የሚቆራረጥ መሆኑ፣ ተቋሙ በአግባቡ አገልግሎት ያላገኘበትን የነፃ ጥሪ ማዕከል የወር ክፍያ እስከ 3500 ብር በወር የሚከፍል መሆኑ፤
  - ➢ የነጻ ስልክ ጥሪው በተለያ ቋንቋ አቤቱታ ለመቀበል 18 ባለሙያ የሚያስፈልግ ቢሆንም በቦታው ሰው በመመደብ ማዕከሉን እየተጠቀመበት አለመሆና፣ በፈረቃ በመደበኛ ስራቸው ላይ ደርበው በሚሰሩ ሠራተኞች የሚከናወን መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቃለመጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ፣ በነባራዊ ሁኔታ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ

- ከሐምሌ 1/2016 ጀምሮ Case management System ስራ ላይ ተገብቷል ስልጠና ተሰጥቶበት ነው ወደ ስራ የተገባው፣
- የጥሪ ማዕከሉ እንደ ተቋም በነፃ ቁጥር 9503 አገልግሎት ይሰጥ ነበር በቅድሚያ 7502 ነፃ ቁጥር ነበረ ቴሌ በመሃል መጥቶ መቀየር አለባችሁ በማለት ነው የተቀየረው አሁን ላይ እየሰራ አይደለም፣ ቴሌ በምን ምክንያት እንደሚቆራርጥብን ግልፅ አላደረገልንም፣

- የጥሪ ማዕከሉ የቴሌና የሲቪል ሰርቪስ እጅ ላይ ያለ ጉዳይ ነው ምክንያቱም የሲቪል ሰርቪስ በዚህ አመት ማንም ሰራተኛ መቅጠር የለባችሁም ስለተባልን፣
- የሲስተሙ ስራ በተቋሙ የምርመራ ማንዋል ላይ ማንኛውም አቤቱታ ተቀባይ ወይም የሚመጡ አቤቱታዎች በኬዝ ማኔጅመንት ሲስትም ውስጥ እንዲመዘገቡ አስገዳጅ መሆኑ፣ እና ይህም ተግባራዊ ሰለመሆኑ ክትትል እንደሚደረግና ሪፖርት እንደሚቀርብ፣እነዚህ ከተቋሙ አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች መሆናቸውን የኦዲት ቡድኑ ግንዛቤ ውስጥ ቢገባ፣ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

47. ኃላፊዎች ይህን ምላሽ ቢሰጡም የኬዝ ማኔጅመንት ሲስተሙ በስምንቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከዋናው መ/ቤት ጋር እኩል መስራት እንዳለበት ቢገለጽም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሲስተሙን ለመተግበር የሰው ኃይልና እንፍራስትራክቸር ባለመሟላቱ እየተጠቀሙበት አለመሆኑ፡፡ እንዲሁም አዲሱ የጥሪ ማዕከል ሥራ ላይ የዋለው በ2012 ዓ.ም.በመሆኑ እና በ2017ዓ.ም. ሰው መቅጠር አይቻልም ስለተባለ ነው ያልተቀጠረው የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

48. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አሰራሩና አግልግሎት አሰጣጡ በተሟላና ዘመናዊ ለማድረግ ሀብት የፈሰሳባቸውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ አለማዋል የአቤቱታና የቅሬታ አቀባበሉን ቀልጣፋ የማያደርገው እና ዘመናዊ አሰራሮች ወደ ተቋሙ እንዳይገባ በማድረግ መ/ቤቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዳይፈጽም እንቅፋት ይሆናል፡፡

## በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን በሚመለከት ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፣

49. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከልና ደርሶም ከሆነ ለማረም በመንግሥት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል

50. ይሁን እንጂ

    - ✓ በ2016 በጀት አመት ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተመለከቱ ስራዎች ለማከናወን በእቅድ የተያዘና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የቀረበ ቢሆንም የታዩና ክትትል ከተደረገባቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት የተገኙትን ደካማ ጎኖች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ያልተገበሩ ተቋማት በድጋሚ ቁጥጥር ወቅት የተገኙ መሆኑ እና በነዚህ ተቋማት ላይ የተወሰደ

እርምጃን የተመለከተ  የቁጥጥር ግኝቶችን በማይፈፅሙ ተቋማት ላይ የማስጠንቀቂያ ወይንም ለሚመለከከተው አካል ተቋሙ ስለማሳወቁ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩ፣

በኦዲት ወቅት ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ላይ በሰጡት ምላሽ ተቋማችን ቁጥጥር ለማድረግ ስናቅድ በጉዳይና በተቋም በመሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

52. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም  በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከልና ደርሶም ከሆነ ለማረም እንዲሁም በህግ የተቀመጡ ድጋፎች እና መብቶች መሰረተ ልማቶች ካልተሟሉ እነዚህ የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚደርሱ አስተዳደራዊ በደሎች መቀረፋቸውን እና እንደማንኛውም ዜጋ አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አዳጋች  አድርጓል፡፡

## ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫና ሥልጠና መገምገሙን በተመለከተ

53. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዜጎች ላይ አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ሊሰጥና ግንዛቤው ያስገኘውን ፋይዳ ሊገመግም ይገባል፡፡

54. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ✓ ተቋሙ ግንዛቤ ለመስጠትና ግንዛቤ ለመፍጠር ከተለያዩ የክልልና የአካባቢ ሬድዮ ጣቢያዎች ጋር የፕሮግራምና ማስታወቂያዎች ስርጭት ለማከናወን ውል የገባ መሆኑ፣
- ✓ ተቋሙ ማህበራዊና ብዙ የማህበረስብ ክፍሎች የሚጠቀሙበትን ሚዲያ (ማለትም ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ኤክስ (የቀድሞው ትዊተር) ቻናሎችን እና የመሳሰሉትን በመጠቀም የሚያከናውናቸውን ተግባራት ተደራሽ እያደረገ መሆኑ፤ ነገር ግን
- ✓ የተሰጡ ሥልጠናዎችና ግንዛቤዎች ያስገኙት ፋይዳ አልመገምገሙ

በኦዲት ወቅት ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

55. ስለጉዳዩ የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ በነባራዊ ሁኔታ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ  በመረጃ ነጻነት ህግ ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መሰጠቱን፣ እንዲሁም በ2015 ዓ.ም በዓመቱ ተቋሙን የተመለከቱና ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ላይ መሰረት ያደረጉ 9 የሬዲዮ ማስታወቂያዎች ተዘጋጅተው በ 40 ሚዲያዎች በ 19 ቋንቋዎች ለ 5360 ጊዜ መሰራጨታቸውን፣ በቴሌቪዥን፣ በሬድዮ፣ በህትመትና የማህበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ግንዛቤ መሰጡን ገልጸዋል፡፡ የተሰጡት ግንዛቤ ስለመገምገሙ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

56. በዜጎች ላይ የአስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ ለህብረተሰቡና ለአስፈፃሚ አካላት/ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት በዕቅድና የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የተሰጡ ግንዛቤ የማስጨበጫ እና ሥልጠናዎች  ያስገኙት ፋይዳ ካልተገመገመ የተቋሙ ኃላፊነትና ህብረተሰቡን በምን በኩል ድጋፍ ሊያደርግለት የሚችል አደረጃጀት መኖሩን እንዳይረዳና የሚሰጡት ግንዛቤዎች ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳይታወቅ የሚያደርግና ማህበረሰቡ በአግባቡ ከተቋሙ አንዳይጠቀም ወይንም ከኃላፊነቱ ውጭ አገልግሎት እንዲጠይቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች  መሰራጨታቸውን እና ግንዛቤዎቹ ያስገኙትን ውጤት በየጊዜው መገምገሙን  በተመለከተ፤**

57. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያሰራጭ እና የተሰጡ ግንዛቤዎች ያስገኙትን ውጤት በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ 590/2000 መሰረት የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችንና ማብራሪያዎችን በማሳተም እያሰራጨ አለመሆኑ፤
- የመረጃ ነፃነት አዋጅ 590/2000 አንቀፅ 32 ላይ ለሚመለከታቸው አካላት የሚሰጡ  ግንዛቤዎች ያስገኙትን ውጤት  በየጊዜው  የሚገመግምበት ስርዓት የሌለው መሆኑ
- ከዋና መ/ቤት ጀምሮ እስከ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በሚሰራቸው የመረጃ ነፃነት

አዋጅ (590/2000 አንቀፅ 32) ከማስተግበር አኳያ ችግር የሚስተዋልበት መሆኑ፣ <u>**ምሳሌ፡-**</u> ከመረጃ ነጻነት አንጻር መረጃ ማግኘት ህጋዊ መብት ቢሆንም በአፈጻጸም ዙሪያ ቅሬታ አቅራቢዎች የተወሰነላቸዉን ውሳኔ በወቅቱ የማያገኙ መሆኑ፣

- ❖ የመረጃ ነፃነት ሕግን ለማስፈፀም በፊት ለፊት መድረኮች እና በመገናኛ ብዙሃን ሲያከናውናቸው የነበሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተደራሽ ያለመሆናቸው፣
- ❖ የመረጃ ነፃነት ሕግ በአገራችን ተግባራዊ እንዲሆን በተቋማት ላይ የሚያደርገው ክትትልና ድጋፍ ውጤታማ አለመሆኑ፣
- ❖ የመረጃ ነፃነት ሕግ አተገባበር ላይ ከተለያዩ ተቋማት ሪፖርት በመቀበል ወቅታዊ ግብረ-መልስ የማይሰጥ መሆኑ።

ለኦዲቱ ቀርበው፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

59. ስለሁኔታው የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ የተሰጠን ስልጣን ክትትል የማድረግ ነበር አሁን ላይ ግን በተሻሻለው አዋጅ የመቆጣጣር ስልጣንም ተሰጥቶታል በመረጃ ነፃነት ዙሪያ ያስገኙትን ውጤት ከተገመገመ በኋላ የአዋጅ ማሻሻያ ግብአት እንዲሆን ተደርጓል እንዲሁም ከዚህ ጋር የተያያዙ 12 የሚሆኑ መመሪያዎችን አውጥተናል መመሪያዎቹ በማለት ገልፀዋል፡፡

60. የመረጃ ነፃነት ህጎችን-በመውጣት ለአስፈፃሚ ተቋማት እና ለሚመለከታቸው አካለት በማሰራጨት በሃገሪቷ የሰዎች መረጃ የማግኘት መብት እንዲረጋግጥ የማስቻል እና በመንግሥት አሰራር ላይ ግልፅነት እና ተጠያቂት እንዲረጋገጥ አስተዋፅዎ በማድረግ ላይ ውስንንነት እንዲኖር አድርጓል፡፡

## ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

61. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የተቋሙን አገልግሎት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሠራ፣ አብሮ ሊያቅድና አፈጻጸሙንም የሚገመግምበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል

62. ይሁን እንጂ፡-

- ❖ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ አለመሆን፣

- ❖ ከሚመለከታቸው የዴሞክራሲ ተቋማት  ትስስር ያልተፈጠረ መሆኑ፣
- ❖ ለህብረተሰቡ፣ ለአስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት በገፅ ለገፅ መድረኮች፣ በልዩ ልዩ ሚዲያዎችና የኮሚዩኒኬሽን ስልቶች ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ መረጃዎችን አለማድረስ፣
- ❖ ከፌዴራልና ከክልል እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ለኦዲቱ ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡

63. ስለሁኔታው የተቋሙ የስራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት ምላሽ ከባለድርሻ አካላት፣ ከዴሞክራሲ ተቋማት፣ ከሚዲያ ተቋማት፣ ከህዝብ ቅሬታ ሰሚ አካላት፣ በመልካም አስተዳደር እና በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰራ እንደሚገኝ እንዲሁም ተቋማችን የዓለምአቀፍ እና የአፍሪካ ዕንባ ጠባቂዎች ማህበር አባል ሲሆን በጋራ እየሰራ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

64. የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ላይ ሲገልፁ ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ አለመሆን በተመለከተ ለተገለጸው፡ ተቋማችን ከባለድርሻ አካላት ፣ ከዴሞክራሲ ተቋማት፣ ከሚዲያ ተቋማት፣ ከህዝብ ቅሬታ ሰሚ አካላት ፣በመልካም አስተዳደር እና በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም ተቋማችን  የዓለም አቀፍ እና የአፍሪካ ዕንባጠባቂዎች ማህበር አባል ሲሆን በጋራ እየሰራ ይገኛል ከክልል ምክር ቤቶች፣ ከሚዲዋዎች እንዲሁም ከህዝብ ግንኙነት ማህበር ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል መረጃው ይቀርባል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

65. የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም ከዲሞክራሲ ተቋማት ጋር በቅንጅት የተሰራበት፣ የታቀደበት እና ሥራዎች በጋራ የተገመገሙበት ማስረጃ ባለመቅረቡ ምክንያት በነባራዊ ሁኔታ ላይ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

66. የተቋሙ ስራ በሁሉም አገሪቷ ክፍል ተደራሽ እንዲሆን እንዲሁም ከሚመለከታቸው ዲሞክራሲ ተቋማት ጋር በጋራና  በቅንጅት እየሰራ ባለመሆኑ ምክንያት በፍጥነትና በተዓማኒነት መልኩ መልካም አስተዳደር እንዳይስፋፋ አድርጓል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

67. በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መንገድ እየተሰራ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች እና ክፍተቶች ተገኝተዋል፡

❖ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1142/2011 ማስፈጸሚያ ረቂቅ ደንብ በሐምሌ 2012 ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቢላክም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመጽደቁ፣

❖ አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የህግ ማዕቀፍ ማለትም የማቋቋሚያው አዋጁንም ሆነ በተደራቢነት የተሰጠውን የመረጃ ነፃነት የሚደነግገው አዋጅ 590/2000 አንቀፅ 32 ላይ ያለውን የማስፈፀም የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ አለመጽደቁ፣

❖ ተቋሙ በተሰጠው ስልጣን ተግባር መሰረት በራስ ተነሳሽነት ምርመራ ለማከናውን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ቢታቀድም በእቅድ መሰረት በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ በራስ ተነሳሽነት ምርመራ አላካሄደም፣

❖ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ የሚያስችል የሚያከናውናቸው ጥናቶች እንዲጠቀሙበት ለሚመለከታቸው አካላት ስለመላኩ ስለመከናወኑ ማስረጃ ተጠይቆ አልቀረበም፣

❖ በአስተዳደር በደልም ይሁን በሴቶች፣ ህፃናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ከሚመለከታቸው ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት ወይም በቅንጅት እየሰራ ስለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፣

❖ ተቋም አሰራሩና አገልግሎት አሰጣጡ በተሟላ መልኩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (ICT) ለማስደገፍ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል በተከፈለ በብር 7,541,016.21 የተዘረጋው በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ የሚመዘገብበት ሲስተም ማለትም (Case management System) አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ማለትም ከዋና መ/ቤቶች እስከ ስምንቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

❖ በ2012 ዓ.ም የጥሪ ማዕከል (Call Center Hosting Service Contract) የኢትዮ ቴሌኮም እና ከህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ከቻይና ከመጣ ተቋም IPCC (Internet Protocol Contact Center) የሚባል የጥሪ ማዕከል (7502) አገልግሎት ለማግኘት በብር 1,078,743.59 ውል ተዋውሎ ወደ ተቋሙ ያስገባ

ቢሆንም ተቋሙ ባለሙያ በመመደብ ማዕከሉን እየተጠቀመበት አለመሆኑ፣ ይህ ሥርዓት በ2015 ዓ.ም Web-Sprix በተባለ አገር በቀል ሶፍት ዌር አምራች የተመረተ IP-PBX (9503 ነፃ የስልክ ጥሪ) የተባለ የጥሪ ማዕከል ተግባራዊ ማድረጉን ግን አገልግሎቱ የሚቆራረጥ መሆኑ፣ ለነጻ ስልክ ጥሪ የሚቀበሉ ቋሚ ባለሙያዎች የሌለው መሆኑ፤

- ❖ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዜጎች ላይ የአስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ ለህብረተሰቡና ለአስፈፃሚ አካላት/ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ያስገኙት ፋይዳ አልተገመገም፤
- ❖ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ 590/2000 መሰርት የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ህጎች፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችንና ማብራሪዎችን በማሳተም በአግባቡ እያሰራጨ አይደለም፣
- ❖ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ አለመሆን

ናቸው፡፡

68. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

69. በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል የአቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ተቋሙ በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው የተዘጋጁት ረቂቅ ደንቦች እንዲጸድቁ በየጊዜው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ሊያስብና ሊከታትለ የሚገባና ከተዘጋጀ አምስት አመት የሆነው ረቂቅ ደንብን ደግሞ በተሻሻለው የተቋሙ አዋጅ መሰረት በፍጥነት በማሻሻልና የባለድርሻ አካላትን ግብዓት በማሰባሰብ እንደገና ለምክርቤቱ በመላክ ሊያጸድቅና ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
- በሀገሪቷ መልካም አስተዳደር ለማስፈንና የዜጎችን እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም በመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት ያለውን አሰራር በመዳሰስና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በህብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን ሊያሰባስብ ይገባል፡፡ እንዚህንም መሰረት በማድረግና የቅርንጫፍ ጽቤቶቹን አቅም ያገናዘበ ዕቅድ በማውጣት በራስ ተነሳሽነት ምርመራ ሊያካሂድ እና የመፍትሔ ሃሳብ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሳውቅ እንዲሁም ውጤቱን ለህብረተሰቡ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡
- በተቋሙ የሚከናወኑ የአስተዳደራዊ በደል አቀባበል፣ ምርመራ እንዲሁም ምላሽ አሰጣጥ የአሰራር ግድፈቶችን ለመቅረፍና የተሻለ አሰራሮችን ለማምጣት በእቅድ በመታገዝ የሚከናወኑ ችግር ፈቺ ጥናቶች ጥናቱ ለተከናወነባቸው ተቋማት እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ሊደርስና ወደ ተግባር እንዲገቡ ሊያደርገና አፈጻጻማቸውን ሊከታተል የሚገባና የጥናቱን ውጤት ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል ያስችል ዘንድ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ልዩ መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችልና ተግባራዊ የሚሆን ጥናት የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በተለይም የእነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎችን ከሚወክሉ ማህበራትና


አደረጃጀቶች ጋር በመሆንሊሰራ እንዲሁም የተለያዩ ችግሮችን በማጥናት የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡


- አሰራሩና አግልግሎት አሰጣጡ በተሟላና ዘመናዊ ለማድረግ የተዘረጋውን በአቤቱታ ቅበላና ምርመራ የሚመዘገብበት ሲስተም ማለትም (Case management System) አገልግሎት በሙሉ ኃይሉ በሁሉም ቅርንጫፎች ወደ ትግበራ ሊያስገባ እንዲሁም የአቤቱታና ቅሬታ መቀበያ የነጻ ጥሪ አገልግሎትም የ24 አገልግሎት እንዲሰጥ በተፈላጊው የሰው ኃይል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሟሟላት ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡
- በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከልና ደርሶም ከሆነ ለማረም በመንግሥት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በዜጎች ላይ የአስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ ለህብረተሰቡና ለአስፈፃሚ አካላት/ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት በአመታዊ እቅዱ ላይ በማካተት እና የድርጊት መርሃ ግብር በማውጣት ለህብረተሰቡም ግንዛቤ ማስጨበጥና የተለያዩ የስልጠና ማዋሎችን በማዘጋጀት የሚሰጣቸውን ሥልጠና እና ግንዛቤዎች ስገኙትን ፋይዳ ሊገምግም፣ ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ጠንካራ ጎኖቹ የሚጠናከሩበት ደካማ ጎኖቹም የሚስተካከሉበትን ሁኔታዎች ሊያመቻቻል ይገባል፡፡
- በአዋጅ 590/2000 መሰርት የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዩ ህብረተሰብ በአግባቡ እንዲያወቁ ህጎች፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችንና ማብራሪያዎችን በማሳተም እንዲሁም በኤሌክትሮኒክስ ቅጂ ማስራጨት ይጠበቅበታል፡፡
- የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የተቋሙን አገልግሎት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሠራ፣ አብሮ ሊያቅድና አፈጻጸሙንም የሚገመግምበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ፣ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እና በናሙና የታዩ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች፣ የትምህርት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡


## አባሪ 1፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ድርጅታዊ መዋቅር /Organizational Structure/

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና መ/ቤት መዋቅር




የህፃናትና ሴቶች መብቶች አፈፃፀም
የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች
የመልካም አስተዳደር አፈፃፀም ቁጥጥር
የመንግስ ት ፕሮጀክቶ ች
የሕግ ጥሰትና የአስተዳደር በደል አበቴታ ቅበላ
የመንግስት ተቋማት የሕግና
የግል ተቋማት የሕግና አስተዳደር በደል
የመረጃ ነፃነት ህግ ማዕቀፍ ዝግጅት ዴስክ
የመረጃ ነፃነት ህግ ትግበራ ቁጥጥር ዴስክ
የመልካም አስተዳደር ጥናት
የህግ ማሻሻያ ምክረ-

# የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ቅ/ጽ/ቤቶች መዋቅር



## አባሪ-2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም | 1. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸውን አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎች እና አሠራሮቻቸው ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን እንዲሁም ሌሎች ህጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡(**ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር** 1142/2014 **አንቀፅ** 7 **ንዑስ አንቀፅ** 1 |
| | 2. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የህግ ማዕቀፍ ማለትም ደንብ እና የአሰራር መመሪዎች በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡(**ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር** 1142/2014 **አንቀፅ** 44 **ንዑስ አንቀፅ** 1) |
| | 3. ተቋሙ በራስ ተነሳሽነት ወይም በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ስልታዊ ምርመራ ሊያካሂድ ይገባል፡፡ (**ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር** 1142/2014 **አንቀፅ** 7 **ንዑስ አንቀፅ** 2) |
| | 4. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም መፈጸማቸውን ላረጋገጣቸው አስተዳደራዊ በደሎች የመፍትሄ ሀሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡( **ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር** 1142/2014 **አንቀፅ** 7 **ንዑስ አንቀፅ** 3) |
| | 5. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስፈፃሚ አካላት በሚያከናውኗቸው ሥራዎች በሕግ መሠረት የሚያከናውኑ መሆኑን ለማረጋገጥ እና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ ለመከላከል የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡( **ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር** 1142/2014 **አንቀፅ** 7 **ንዑስ አንቀፅ** 4) |
| | 6. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ የሚያስችል ጥናት ሊያጠናና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡( **ምንጭ፡- አዋጅ ቁጥር** 1142/2014 **አንቀፅ** 7 **ንዑስ አንቀፅ** 5) |
| | 7. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የቅሬታ፣ የምርመራና የውሳኔ ሰነዶች የሚጠበቁበትና የሚወገዱበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ (ምንጭ፡-አዋጅ ቁጥር 590/2000 አንቀፅ /38 /ንዑስ አንቀፅ 1 |
| | 8. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በቁጥጥር የተለዩ አላሰራ ያሉ የሕግ ማነቆዎች እና ተደጋጋሚ የአስተዳደር ጥፋቶች የሚከሰቱበትን ምክንያቶች በማጥናት ለምክር ቤቱ ልዩ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡(**ምንጭ፡-የተሻሻለ የቁጥጥር አሠራር መመሪያ ገፅ**-10)1 |
| | 9. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተለይ በሕጻናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከል የሚያስችል ጥናት በማስጠናት ተግባራዊ ሊያደርግይገባል፡፡(**ምንጭ፡-የተሻሻለ የቁጥጥር አሠራር መመሪያ ገፅ**-10)1 |

| | |
|---|---|
| 2. ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር አስተዳደራዊ በደል አቤቱታ አቀባበል፣ምርመራ እና ምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እና መረጃ አያያዝ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ | 10. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተለዩት የህግና የአሰራር ክፍተቶች በተሰጣቸው ምክረ ሃሳብ መሰረት ተግባራዊ በማያደርጉ አስፈፃሚ አካላት ላይ ክስ እንዲመሰረት ሊያደርግ ይገባል፡ **(ምንጭ፡-የተሻሻለ የቁጥጥር አሠራር መመሪያ ገፅ-10)** |
| | 11. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የአስተዳደራዊ በደል አቀባበል፣ምርመራና ምላሽ አሰጣጡ በተሟላ መልኩ በICT እንዲታገዝ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የ10 አመት መሪ እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም ገፅ -52)4** |
| | 12. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በሕጻናት፣ በሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ አሰተዳደራዊ በደሎችን ለመከላከልና ደርሶም ከሆነ ለማረም በመንግሥት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የዜጎች ቻርተር ገፅ-7)2** |
| | 13. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዜጎች ላይ አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የ10 አመት መሪ እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም ገፅ-52፣የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የዜጎች ቻርተር ገፅ-9፣አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 7)** |
| | 14. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ የመረጃ ነፃነት መብትን የተመለከቱ ህጎች፣አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችንና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያሰራጭ እና የተሰጡ ግንዛቤዎች ያስገኙትን ውጤት በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-በአዋጅ 590/2000 አንቀፅ 32፣የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የዜጎች ቻርተር ገፅ-11)** |
| | 15. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የተቋሙን አገልግሎት ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች እና አስፈጻሚ አካላት ተደራሽ የሚያደርግበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የ10 አመት መሪ እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም ገፅ -62)2** |
| | 16. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የተቋሙ ተልዕኮ እንዲሳካ ለማድርግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡- የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የ10 አመት መሪ እቅድ ከ2013-2022 ዓ.ም ገፅ -62)2** |
| | 17. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት ለሚገኙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ)** |
| | 18. የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተቋሙ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ተግባራዊ ስለመደረጉ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ **(ምንጭ፡-የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የ5 አመት መሪ እቅድ ከ2013-2017 ዓ.ም ገፅ -8)** |

## አባሪ 3፡ መጠይቅ የቀረበላቸው መ/ቤቶች ዝርዝር

❖ **የፌዴራልና አስፈፃሚ ተቋማት፣**

1. ጤና ሚኒስቴር
2. ትምህርት ሚኒስቴር
3. ማዕድን ሚኒስቴር
4. የኢትዮጵያ ስብዓዊ መብቶች ኮሚሽን
5. የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባስልጣን
6. አዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ
7. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዮኒቨርስቲ
8. ገቢዎች ሚኒስቴር

❖ **የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ኦሮሚያ ቅርናጫፍ ጽ/ቤት

❖ **መጠይቅ ተልኮላቸው ሞልተው የላኩ የተቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

1. የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም መቀሌ ቅርንጫፍ
2. የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ባህርዳር ቅርንጫፍ
3. የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አሶሳ ቅርንጫፍ
4. የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሃዋሳ ቅርንጫፍ
5. የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም አፋር ቅርንጫፍ
6. የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ጋምቤላ ቅርንጫፍ